# ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው
## ሰባልዮሳውያን ነበሩ ወይስ ሥላሴያውያን?

በተባበሩት ጴንጤቈስጣውያን ዓለም ዐቀፍ ቤተ ክርስቲያን (UPCI) ስመ ጥር ጸሓፊና እንደ ታዋቂ የነገረ መለኮት ምሁር የሚታዩት ዴቪድ ኬ በርናርድ፣ "ዘ ዋንነስ ኦፍ ጎድ" እንዲሁም "ዋንነስ ኤንድ ትሪኒቲ" በሚል ርእስ የጻፏቸው መጻሕፍት፣ ትምህርተ ሥላሴ በቃለ እግዚአብሔርም ሆነ በሥነ አመክንዮ አንጻችም መሠረት የሌለው አስተምህሮ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አበው ሰባልዮሳዊ አስተሳሰብና እምነት ነበራቸው የሚል አቋም አላቸው:: እንደ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት አስተምህሮ ሁሉ ዴቪድ በርናርድም ትምህርተ ሥላሴ ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ የገባ ባዕድ ትምህርት ነው በሚለው ነጥብ ላይ ተመሳሳይ አቋም ይጋራሉ::

እነዚህ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ትምህርተ ሥላሴ በብሉያትም ሆነ በሐዲሳት፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሆነ በሥነ አመክንዮ አንጻችም ድጋፍ የሌለው አስተምህሮ ስለሆነ፣ በ325 ዓ.ም በኒቂያ ከተካሄደው ጉባኤ በፊት የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አበው፣ ይህ ዐይነቱ እምነት እንዳልነበራቸው እንዲሁም ትምህርቱንም እንዳላስተማሩ ይሞግታሉ:: እንዲያውም የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፣ ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው አርዮሳዊ አስተሳሰብ ነበራቸው የሚል አቋም ያለው ሲሆን፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም የተባበሩት ጴንጤቈስጣውያን (UPCI) በመባል የሚታወቁት የሃይማኖት ድርጅቶች ደግሞ፣ ከኒቂያ በፊት የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሰባልዮሳዊ አቋምና አስተምህሮ ነበራቸው ባዮች ናቸው::

እነዚህ የሃይማኖት ድርጅቶች ከኒቂያ ጉባኤ በፊት በነበሩት የቤተ ክርስቲያን አበው ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደረጉበት ምክንያት፣ የሥላሴ ትምህርት መሠረቱን የጣለው ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ ነው የሚለውን አስተምህሮአቸውን እንዲደግፍላቸው በጽኑ በመፈለጋቸው ነው::

ሥላሴውያን ደግሞ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ "ውጉዝ ከመአርዮስ ወውጉዝ ከመሰባልዮስ" ካሉት ከኒቂያ ጉባኤ አባቶች ቅንጣት ታህል የተለየ አቋምም ሆነ አስተምህሮ እንዳልነበራቸው እንዲሁም በየዘመኑ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ይህን መሠረተ እምነት ይዛ እንደ ቀጠለች ያስረዳሉ::

እውነቱ በየት ወገን ነው ያለው የሚለውን ጉዳይ በማያወላዳ መልኩ ለመመለስ፣ ሁለት አቅጣጫዎችን መከተል የግድ ይሆናል:: ይኸውም:— (1) የድርጅቱ ዕውቅ መምህራን ከአበው ጽሑፍ በቀጥታ ጠቅሰናቸዋል የሚሏቸውን ማስረጃዎች በቅርበት መመርመር፣ (2) በሁሉም ወገኖች ዘንድ ተኣማኒና ነጻ መረጃ ናቸው የሚባሉትን የእነዚህን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ድርሳናት በቀጥታ በመጥቀስ እውነታው በየት ወገን እንዳለ ማሳየት ነው::

## I. ሥላሴ ከአረማውያን አስተሳሰብ የተቀዳ ነውን?

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍያን አስተምህሮተ ሥላሴ:— (1) ከአረማውያን መድብለ አማልክት አስተሳሰብ የተቀደ ነው፤ (2) ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ሰባልዮሳዊ አስተሳሰብና እምነት ነበራቸው የሚል አቋም አላቸው::

ዴቪድ ኬ በርናርድ የተባሉት ታዋቂ የድርጅቱ የነገረ መለኮት መምህር የጥንት አሳራውያን፣ ባቢሎናውያን፣ ግብፃውያን፣ የሂንዱና የታኦይስት ሃይማኖት እንዲሁም አፍላጦናዊው ፍልስፍና የሥላሴ አስተምህሮ እንዳላቸው፣ "ስለዚህም የሥላሴ አስተሳሰብ ከክርስትና አስተምህሮ ውስጥ የበቀለ ሳይሆን፣ የአረማውያን ሃይማኖትና ፍልስፍና ዐይነተኛው ገጽታ ነው..."[1] የሚል አቋም አላቸው። "እነዚህ ቀደምት ነገረ መለኮታውያን ይህ ዐይነቱን ጭፍን ስሕተት እንዴት ሊሠሩ ቻሉ? ያለፈውን ታሪካቸውንም ሆነ ባህላቸውን ከአረማውያን አስተሳሰብ ማራቅ ተስኖአቸዋል"[2] ሲሉም ይወቅሳሉ።

ይህ የዴቪድ በርናርድ ሒስ ሁለት መሠረታዊ ስሕተቶች አሉበት:— (1) በርካታ አረማውያን ሥላሴ መሰል አስተሳሰብ አላቸው የሚለው እሳቤ፣ አስተምህሮተ ሥለሴ አረማዊ መሠረት አለው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርሰን አይችልም—ይህ ለመሆኑ አጥጋቢ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር። በርካታ አረማውያን ዓለማት ፈጣሪ እንዳላቸው ያምናሉ። ይህ ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና ይህን አስተምህሮ የቀዳው ከአረማውያን ነው ማለት ስሕተት ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ባህላዊ ሃይማኖቶች ለኀጢአት ሥርየት ደም መፍሰስ አለበት የሚል እምነት አላቸው። እነዚህ ባህላዊ ሃይማኖቶች ይህ ዐይነቱ እምነት አላቸው ማለት፣ ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም የሚለው የብሉያትና የሐዲሳት መሠረተ እምነት ከባህላዊ ሃይማኖቶች የተቀዳ ነው ማለት ስሕተት ነው (ለመቀዳቱ ተጨባጭና ተአማኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ)።

(2) የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን አሶራውያን፣ ባቢሎናውያን፣ ግብፃውያን ወዘተ ሥላሴያዊ አስተሳሰብ አላቸው ይበሉ እንጂ እነዚህ አረማዊ ሃይማኖቶችና ፍልስፍናዎች የሦስት አማልክትነት አስተሳሰብ ያለው የመድብለ አማልክት አቋም እንጂ፣ ሥላሴያዊ አስተምህሮ ያላቸው አይደሉም[3]። ዴቪድ በርናርድ ሥላሴያውያን፣ "ታሪካቸውንም ሆነ ባህላቸውን ከአረማውያን አስተሳሰብ ማራቅ ተስኖአቸዋል" የሚለው ወቀሳቸውም አስተምህሮተ ሥላሴ ከአረማውያን አስተሳሰብ የተቀዳ ነው የሚለውን እሳቤ ታሳቢ ያደረገ እንጂ ለጉዳዩ ተጨባጭና አሳማኝ ማስረጃ ያቀረበ አይደለም። እንዲያውም ከሥላሴ አስተምህሮ ይልቅ አረማዊ ሃይማኖቶችና ፍልስፍናዎች ጋር የሚመሳሰለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ነው። ለምሳሌ የሂንዱ ፍጹምና የማይከፋፈለው አምላክ ብርሃማን ራሱን በሦስት መንገዶች ገልጾአል *ብርሃማ* እንደ *ፈጣሪ*፣ *ቪሽኑ* እንደ *ጠባቂ* እንዲሁም *ሺቫ* እንደ *አጥፊ*። ይህ የሂንዱ ሃይማኖት አስተምህሮ፣ በዘመን ብሉይ አብ የነበረው አምላክ በዘመን ሐዲስ ወልድ እንዲሁም በባለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ሆኖ መጣ ከሚለው ከሰባልዮስ አስተምህሮ ጋር እንጂ፣ ከሥላሴ ትምህርት ጋር በጭራሽ የሚመሳሰል አይደለም።

## II. ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ሰባልዮሳዊ እምነት ነበራቸውን?

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፍ ቢሮ ታዋቂ የነገረ መለኮት መምህር የሆኑት ዴቪድ ኬ በርናርድ፣ ትምህርተ ሥላሴ ከአረማውያን ሃይማኖትና ፍልስፍና የተቀዳ ባዕድ ትምህርት ነው የሚል አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፣ ጥንታውያኑ የቤተ ክርስቲያን አበው ሰባልዮሳዊ ሃይማኖታዊ አቋም ነበራቸው የሚልም ሙግት አላቸው:—

---

[1] David K. Bernard, *The Oneness of God* (Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1983), 164-65.
[2] ዝኒ ከማሁ፣ 176።
[3] Benjamin B. Warfield, "Trinity," in *The International Standard Bible Encyclopedia,* ed. James Orr et al., 5 vols. (1956, reprint; Peabody, Mass.: Hendrickson, 1994), 3012.

"በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ አንድም [ክርስቲያን] ጸሐፊ ሥላሴያዊ የሆነውን አስተምህሮ በትክክል አላስተማረም፤ እንዲያውም አንዱ መለኮታዊ አካል ለሌላው እንደሚገዛ በግልጽ በመጻፍ የሥለሴን አስተምህሮ ክደዋል"[4]።

"[የሮሙ] ቀለሜንጦስ [በ100 ዓ.ም ላይ በጻፈው ጽሑፍ][5]. . .አብን ፈጣሪያችን፣ አዳኛችንና ጌታችን አድርጎ አቅርቦታል ይህም የኢየሱስ የማኅረግ ስም ነው"[6]።

"የአግናጢዮስ ጽሑፎች (110-15) ኢየሱስን ከአንዱ አምላክ ጋር ያመሳስሉታል፤ ከዚህም የተነሣ አንዳንድ የታሪክ ምሁራን የአግናጢዮስ አስተምህሮ እንደ ሞዳልስቲክ ነው እንዲሉ አድርጓቸዋል . . . አግናጢዮስ ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ እንደ ሆነ ገልጾአል. . . አግናጢዮስ አምላክ ሲል አብን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ስለሆነ. . .ይህ ኢየሱስ ትስብእት የሆነ እግዚአብሔር አብ ነው የሚለውን አስተሳሰቡን ይፋ የሚያደርግ ነው"[7]።

"አግናጢዮስ ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው ሲል በግልጽ ተናግሮአል [በማግኔዢያንስ 15 እንዲህ ይላል፣ 'የማይነጣጠለው መንፈስ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ']"[8]።

"ሔርማስ [*እረኛው* በሚለው ጽሑፉ 140-45] መንፈስ ቅዱስን በግጻዌ መለኮት ውስጥ ራሱን የቻለ አካል አድርጎ አይመለከተውም፤ ራሱን ለዓለም እንደ ገለጠው ልጅ እንጂ፣ 'ቅዱስና ዘላለማዊ (pre-existent) የሆነው መንፈስ ቅዱስ ፍጡራንን ሁሉ የፈጠረ፣ እንደ ፈቃዱ እግዚአብሔር በሥጋ ውስጥ እንዲኖር ያደረገ ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስ የሚያድርበት ሥጋ ለዚህ መንፈስ በከበረ መልኩ ይገዛል' (Sim. 5:6). . . 'መንፈስ ቅዱስን ልገልጥላችሁ እወዳለሁ. . . ይህም መንፈስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው' (Sim. 9:1)"[9]።

"በዮስጦስ የመጀመሪያው አፖሎጂ (c. 150) ላይ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ብዝኃነት እንዳለ አስተምሮአል። በዚህ መሠረት [በመጀመሪያው አፖሎጂ 6 እና 13 ላይ] አብ እውነተኛ አምላክ ነው። ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግን ልክ እንደ መላእክት በሁለተኛ ደረጃ ያሉ አማልክት ናቸው . . . ዮስጦስ ወልድን ከቃል ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ ቃልን ደግሞ ከአብ የተለየ አድርጎ ያቀርበዋል። ወልድ አብ ነው የሚሉ ከአብ ጋር አንዳችም ትውውቅ የላቸውም፤ የዓለማት ፈጣሪ የሆነው አብ ልጅ እንዳለው አያውቁም ማለት ነው፤ ይህም የመጀመሪያ ልጅ የእግዚአብሔር ቃል እንዲሁም እግዚአብሔር ነው"[10]።

---

[4] David K. Bernard, *Oneness and Trinity A.D. 100-300: The Doctrine of God in Ancient Christian Writings* (Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1991), 24.

[5] ዴቪድ በርናርድ ለቀለሜንጦስም ሆነ ለሌሎቹ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተጠቀመው ጊዜ፣ አብዛኞቹ የታሪክና የነገረ መለኮት ሊቃውንት ለእነዚህ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ከተጠቀሙበት ጊዜ ቢያንስ የሠላሳ ዓመት ልዩነት አለው። ሊቃውንት የሮሙ ቀለሜንጦስ ጽሑፉን የጻፈው ቢበዛ 70 ዓ.ም ላይ ከነሰ ደግሞ 68 ዓ.ም ላይ ነው የሚል አቋም አላቸው። በዚህ ረገድ ለምሳሌ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል:— John A. T. Robinson, *Redating the New Testament* (Philadelphia: Westminster, 1976), 352-53.

[6] David K. Bernard, *Oneness and Trinity,* 30።

[7] ዝኒ ከማሁ፤ 33።

[8] ዝኒ ከማሁ፤ 33-34።

[9] ዝኒ ከማሁ፤ 39-41።

[10] ዝኒ ከማሁ፤ 39-41።

> "ምንም እንኳ ዮስጦስ መንፈስ ቅዱስ ከሚመለኩ አካላት መኻል ሦስተኛው አካል አድርጎ ቢያቀርበውም፣ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የተለየ አካል እንደ ሆነ በግልጽ አላስታወቀም፤ እንዲሁም በሦስቱ አካላት ዘንድ ያለውን ግንኙነት አልገለጸም። በርግጥ በበርካታ ቦታዎች ላይ መንፈስን ከቃል ጋር አንድ አድርጓል። ለምሳሌ በመጀመሪያው አፖሎጂው ላይ እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ 'ስሕተት ነው. . .መንፈስንና የእግዚአብሔርን ኀይል የእግዚአብሔር በኵር ከሆነው ከቃሉ የተለየ ማድረግ'"[11]።

> "[የዮስጦስ ደቀ መዝሙር] ታቲያን በመጀመሪያ ቃል በእግዚአብሔር ውስጥ እንደ ነበር ያምናል ይህ እምነቱም ዲያተሰሮን [የወንጌላት ስሙሙነት] የዮሐንስ 1÷1ን 'እግዚአብሔርም ቃል ነበረ' ብሎ እንዲተረጉም አድርጎታል። ይህም አብዛኞቹ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያን ክፍሉን በሚተረጕሙበት መልክ የተተረጐመ ነው። የዐላፊውን ጊዜ ዘላለም በተመለከተ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ዐይነት አመለካከት አለው። ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የሚለየውም ምድር ከመፈጠሯ በፊት በነበረ በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር በመውጣት ከእግዚአብሔር የተለየ አካል ሆኖአል የሚለው እምነቱ ነው"[12]።

"ቅድመ ኒቂያ ጉባኤ አበው አርዮሳውያን ነበሩ ወይስ ሥላሴያውያን?" በሚለው ርእስ፣ የአርዮሳውያኑን ኑፋቄ ይፋ ባደረግንበት መንገድ፣ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሰባልዮሳዊ አቋም እንደ ሌላቸው የሚያስረግጡ በርካታ ምንባባትን ከራሳቸው ጽሑፎች ላይ በቀጥታ በመጥቀስ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን ኑፋቄ ይፋ ማድረግ የሚቻል ቢሆንም፣ እስካሁን ከዴቪድ በርናርድ በቀጥታ የጠቀስናቸው ክፍሎች ራሳቸው፣ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሰባልዮሳዊ አመለካከት ነበራቸው የሚለውን አቋም በጭራሽ የሚደግፍ አይደለም።

እነዚህ ክርስቲያን አባቶች፣ "አንዱ መለኮታዊ አካል ለሌላው ይገዛል" የሚለው አነጋገራቸው፣ የሰባልዮስንም ሆነ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ የሚደግፍ አይደለም እንዲያውም የሚጣረስ እንጂ። ልክ እንደነዚህ የቤተ ክርስቲያን አበው ትምህርት ሁሉ፣ የሥላሴ አማንያንም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ዐይነት ባሕርይ እንዳላቸው ቢያምኑም የፈቃድ መገዛት ግን በሥላሴ አካላት መካከል እንዳለ ከሙሉ ልብ ይቀበላሉ።

የሮሙ ቀለሜንጦስ አብ *ብቻ* ወይም ወልድ *ብቻ* ፈጣሪ፣ አዳኝና ጌታ ነው እስካላለ ድረስ፣ እነዚህ የባሕርይ ስሞች አብን ወይም ወልድን ማሳየታቸው አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ የሚወስደን አይደለም ("አማረ መምህር ነው"። "ተስፋዬ መምህር ነው" ማለት አማረና ተስፋዬ አንድ አካል ናቸው ማለት አይደለም። የመምህርነትን ሥራ ይጋራሉ ማለት እንጂ)።

አግናጢዮስ ኢየሱስ፣ "በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነው" ማለቱ፣ አብ ወልድ ነው የሚል ሰባልዮሳዊ ትምህርት የለውም። የሥላሴ አማንያንም ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነው የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ መሆኑ አምላክነቱን የሚያሳይ እንጂ፣ ኢየሱስ አብ መሆኑን የሚያስተምር አይደለም።

አግናጢዮስ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ነው አላለም። ዴቪድ ኬ በርናርድ በማግኔዢያንስ 15 ላይ መንፈስ ማለቱ መንፈስ ቅዱስ ማለቱ ነው የሚለው ትንታኔያቸው ስሕተት ነው። የመስኩ

---

[11] ዝኒ ከማሁ፤ 68-69።

[12] ዝኒ ከማሁ፤ 79-80።

ሊቃውንት አግናጢዮስ በዚህ ዐውድ መንፈስ የሚለውን ቃል የተጠቀመው *"አመለካከት"* ወይም *"አእምሮ"* የሚለውን ቃል በሚወክል መልኩ ብቻ ነው[13]::

ሊቃውንት ሔርማስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለው አስተምህሮ ግልጽ አይደለም የሚል ሐሳብ የሚጋሩ ቢሆንም እንኳ፣ ሔርማስ ትምህርቱ ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጋር አንድ ዐይነት ነው ወይም ከሥላሴያውን አስተምህሮ ጋር ይቃረናል ማለት ግን አይደለም:: "በኢየሱስ ሥጋ ውስጥ የሚያድረው ዘላለማዊ የሆነው መንፈስ ከኢየሱስ ጋር በጋራ የሚሠራ ነው" (Similitude 5:6) የሚለው የሔርማስ አነጋገር፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ቢያንስ በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን የሚያመለክት ነው::

ዮስጦስ ሰማዕት ስለ ሥላሴ አስተምህሮ የጠራ ትምህርት ነበረው የማይባል ቢሆንም፣ አስተምህሮው ግን አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው የሚለውን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ የሚደግፍ አይደለም:: በርናርድ፣ "በዮስጦስ *የመጀመሪያው አፖሎጂ* (c. 150) ላይ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ብዝኃነት እንዳለ አስተምሮአል" የሚለው ንግግራቸው ዮስጦስ ሰባልዮሳዊ አመለካከት እንደሌለው ግልጽ የሚያደርግ ነው:: ዮስጦስ ሰማዕት፣ "ወልድ የእግዚአብሔር የበኵር ቃል እንዲሁም እግዚአብሔር ነው" (Dialogue with Trypho, 11) ማለቱ የወልድን አምላክነት እንጂ ወልድ ራሱ አባቴ ብሎ የሚጠራው አብ ነው ማለት አይደለም:: በርናርድ ራሳቸው፣ "ዮስጦስ ወልድን ከቃል ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ ቃልን ደግሞ ከአብ የተለየ አድርጎ ያቀርበዋል:: ወልድ አብ ነው የሚሉ ከአብ ጋር አንዳችም ትውውቅ የላቸውም፤ የዓለማት ፈጣሪ የሆነው አብ ልጅ እንዳለው አያውቁም ማለት ነው፤ ይህም የመጀመሪያ ልጅ የእግዚአብሔር ቃል እንዲሁም እግዚአብሔር ነው" የሚለውን የዮስጦስን ንግግር በመጥቀስ አብና ወልድ እንዴት አንድ አካል ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ሊደርሱ ቻሉ? ይህ እርሳቸው የጠቀሱት የዮስጦስ ንግግር አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን እንጂ አንድ አካል መሆናቸውን በጭራሽ አያመለክትም::

ዮስጦስ ሰማዕት፣ "ለእግዚአብሔር ብቻ ልንሰግድ ይገባል" (*የመጀመሪያ አፖሎጂ* 16) እንዲሁም "ለእግዚአብሔር ብቻ ስግደታችንን እናቀርባለን" (*የመጀመሪያ አፖሎጂ* 17) መንፈስ ቅዱስ ሊመለክ የሚገባው አምላክ ነው (*የመጀመሪያ አፖሎጂ* 6) ሲል መንፈስ ቅዱስ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ አምላክ ነው ማለቱ ሳይሆን፣ ልክ እንደ አብና እንደ ወልድ ስግደት የሚገባው አምላክ መሆኑን ለማመልከት ነው (*የመጀመሪያ አፖሎጂ* 6)::

ዮስጦስ ሰማዕት፣ አምልኮ ለመቀበል፣ "የነቢያት መንፈስ" ከአብና ከወልድ ከጥሎ "ሦስተኛ" (*የመጀመሪያ አፖሎጂ* 13) ነው የሚለው አነጋገሩ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ወይም አብና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: በርግጥ በበርካታ ቦታዎች ላይ መንፈስን ከቃል ጋር አንድ አድርጓል:: በርናርድ ዮስጦስ ሰማዕት፣ "በመጀመሪያው አፖሎጂው ላይ እንዲህ ሲል ጽፎአል፣ 'መንፈስንና የእግዚአብሔርን ኀይል የእግዚአብሔር በኵር ከሆነው ከቃሉ የተለየ ማድረግ. . .ስሕተት ነው'" የሚለው አነጋገራቸው መንፈስንና መንፈስ ቅዱስን እርስ በርሱ የሚያምታታ ነው:: ዮስጦስ በዚህ ክፍል መንፈስ ሲል ኑባሬንና (ዮሐንስ 4÷24

[13] E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches* (Reprint, Grand Rapids: Zondervan 1998), 40 ከ J. B. Lightfoot and J. R. Harmer, trans., *The Apostolic Fathers: Revised Greek Texts with Introductions and English Translations* (Reprint, Grand Rapids: Baker, 1984), 146; J. B. Lightfoot, ed. and trans., *The Apostolic Fathers: Clement, Ignatius, and Polycarp, Revised Texts with introductions, Notes, Dissertations, and translations,* 5 vols. (Reprint, Peabody, Mass.: Hendrickson, 1989), 2:2:140. ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

"እግዚአብሔር መንፈስ ነው") ኀይልን ለማሳየት እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስን ለማመልከት አይደለም።

በርናርድ ከታቲያን ጠቅሰው የጻፋትም ጽሑፍ በግልጽ የሚያሳየው፣ ግለሰቡ ሥለሴያዊ አመለካከት እንዳልነበረው ሁሉ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንም መሠረተ እምነት እንደሌለው ነው። ታቲያን ኢየሱስ፣ "ምድር ከመፈጠሯ በፊት በነበረ በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር በመውጣት ከእግዚአብሔር የተለየ አካል ሆኖአል የሚለው እምነቱ" ቄስ ተክሌ በቅርቡ ሰማያዊ ሥጋ በሚል ከጀመሩት ትምህርት ጋር ከሆነ እንጂ፣ ከነባሩ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን (UPCI) አስተምህሮ ጋር የሚዛመድ አይደለም። ነባሩ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ቃል ሥጋ የሆነው በዘመነ ሐዲስ እንጂ፣ "ምድር ከመፈጠሯ በፊት" አይደለምና።

በተጨማሪም ታቲያን በግልጽ ኢየሱስ፣ "ምድር ከመፈጠሯ በፊት በነበረ በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር በመውጣት ከእግዚአብሔር የተለየ አካል ሆኖአል" ማለቱ ግለሰቡ ሰባልዮሳዊ አቋም በጭራሽ እንዳልነበረው የሚያሳይ ነው[14]።

በርናርድ የታቲያንን የዮሐንስ 1÷1 ሐሳብ በተዛባ መልኩ ነው የተረዱት። ይኸውም:— (1) "ቃል ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ነበር" የሚለው የዮሐንስ 1÷1 ሁለተኛ ዐረፍተ ነገር ወልድና አብ አንድ መሆናቸውን (እንደ በርናርድ አነጋገር፣ "ቃል በእግዚአብሔር ውስጥ እንደ ነበር") ሳይሆን አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያስተምር ነው። (2) በርናርድ የዮሐንስ 1÷1 ሦስተኛ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ያለበት፣ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ተብሎ ሳይሆን፣ "እግዚአብሔርም ቃል ነበር" ተብሎ ነው የሚለው አቋም የግሪክን ሰዋሰው በቅጡ ያገናዘበ አይደለም። ይህ የበርናርድ አቋም "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል ባለቤት ሙያ (Subjective) "ቃል" ደግሞ ተሳቢ/አንቀጽ ባለቤት ሙያ (Predicate nominative) ነው የሚለውን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ ነው። ነገር ግን በዮሐንስ 1÷1 "እግዚአብሔር" ተሳቢ ባለቤት ሙያ፣ "ቃል" ደግሞ ባለቤት ሙያ ነው[15]። የታቲያንን የግሪክ ቅጅ ወደ የተረጐሙ ሊቃውንት ራሳቸው ይህን የታቲያንን ሐሳብ የተረጐሙት በዚሁ መልክ ነው[16]። "እግዚአብሔርም ቃል ነበረ" የሚለው ትክክልኛ ትርጉም ነው እንኳ ቢባል፣ ቃል አብ ነው የሚል ትርጉም ሊኖረው አይችልም፤ ምክንያቱም ቃልና እግዚአብሔር አብረው ስለነበሩ እንዲሁም በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ላይ ያለው እግዚአብሔር (θε□ς ቴዎስ) ውስን መስተኣምር (τ□ν) ያለው ሲሆን፣ በሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ላይ ያለው እግዚአብሔር (θε□ς) ግን ውስን መስተኣምር የሌለው መሆኑ በግሪክ ሰዋስው የመጀመሪያው ቴዎስና ሁለተኛው ቴዎስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

---

14 ታቲያን ኢየሱስ፣ "ምድር ከመፈጠሯ በፊት እንኳ ከአብ የተለየ ማንነት ነበረው" የሚል አቋሙን ከሚከተሉት መጻሕፍት ላይ ይመልከቱ:— የታቲያንን *Pros Hellenonas* (ለግሪካውያን የተደረገ ንግግር), 5, in J.P. Mign', ed., Patralogiæ Græcæ, 6:818-15 ከሚከተለው መጽሐፍ ጽሑፍ ጋር ያወዳድሩ:— J.E. Ryland translation in Alexander Robers and James Donaldson, eds., The Ante-nicene Fathers: Translations of the Writings of the Fathers down to A. D. 325, 10 vols. (Reprint, Grand Rapids: Eerdmans, 1975), 2:67.

15 ዮሐንስ 1÷1 በቀጣዮቹ የትምህርት ጊዜያት በስፋት የምንመለከተው ጉዳይ ይሆናል።

16 E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches*, 42 ከ D. Plooij, A Primitive Text of the Diatessaron: The Liege Manuscript of a Mediæval Dutch Translation, A Preliminary Study (Leyden: A. W. Sijthoff's Uitgeversmaatschappij, 1923), introductory note by J. Rendel Harris, 3. ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

# III. ውጉዝ ከመሰባልዮስ!

ዴቪድ ኬ በርናርድን ጨምሮ በርካታ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍያን[17] ቅድመ ኒቂያ ጉባኤ አበው ሰባልዮሳውያን ናቸው የሚል ትምህርት እያስተማሩ ቢገኙም እውነታው ግን እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሰባልዮሳውያን ሳይሆኑ፣ "ውጉዝ ከመአርዮስ ወውጉዝ ከመሰባልዮስ" ካሉት ሥላሴያውያ አበው ቅንጣት የተለዩ ላለመሆናቸው የራሳቸውን ጽሑፎች በቀጥታ በመጥቀስ እውነታውን እንመልከት::

በዚህ ስፍራ በእማኝነት የምንጠቅሳቸው አበው ዋና ዋና የሚባሉ ሐዋርያዊ እንዲሁም በሁለተኛውና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩትን ቀደምትና ደኅርት የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ነው::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍትም ሆኑ ሥላሴያውያን አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ[18]፣ አብ እግዚአብሔር ነው[19]፣ ወልድ እግዚአብሔር ነው[20] እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው[21] በሚለው ነጥብ ላይ አንድ ዐይነት እምነት ቢኖራቸውም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው ወይስ አይደሉም በሚለው ነጥብ ላይ ግን ይለያያሉ:: ስለዚህ እኛ ትኩረት የምናደርገው ከዚህ ቀጥለን የምንጠቅሳቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጽ ማስተማራቸውን ነው:: ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አበው ሥላሴያውያን እንጂ ሰባልዮሳውያን ሊሆኑ አይችሉም::

አግናጢዮስ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን[22] እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

"በልዑሉ አብ እንዲሁም በልጁ በኢየሱስ ክርሰቶስ ቸርነት" (Romans, inscription)

---

[17] **ለምሳሌ** William B. Chalfant, *Ancient Champions of Oneness: A History of the True Church of Jesus Christ* (Junction City, Kans.: 1979).

[18] **ለምሳሌ ቀለሜንጦስ ዘሮም፤ *ቆሮንቶስ*** 58፤ ***ማግኔዢያንስ*** 8፤ **ሔርማስ** *The Shepherd,* Mandate 1, in Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* 82, 144, 422. E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches,* 48 **ጠቅሶ እንደ ጻፈው::**

[19] **ለምሳሌ ቀለሜንጦስ ዘሮም፤ *ቆሮንቶስ*** 62፤ **አግናጢዮስ ኤፌሶን** inscription; **ጶሊቃርጶስ ፊልጵስዩስ** 12፤ in Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* 84 (English), 39 (Greek), 137 (English), 105 (Greek), 181 (English), 173 (Latin). E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches,* 48 **ጠቅሶ እንደ ጻፈው::**

[20] **ለምሳሌ** Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* **ቀለሜንጦስ ዘሮም፤ *ቆሮንቶስ*** 16 (English, p. 63, and Greek, p. 12); **አግናጢዮስ *ኤፌሶን*** inscription (English, 137, and Greek, 105), 1:1 (English, 137, and Greek, 105), 7:2 (English, 139, and Greek, 107), 18:2 (English 141, and Greek, 110), ***ሮሜ*** inscription (English, 152, and Greek, 122), **ጶሊቃርጶስ** 3:2 (English, 160, and Greek, 132), 8:2 (English, 162, and Greek, 134). E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches*, 49 **ጠቅሶ እንደ ጻፈው::**

[21]**ለምሳሌ** Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* **ቀለሜንጦስ ዘሮም፤ *ቆሮንቶስ*** 58 (English, p. 82, and Greek, p. 36); Lightfoot, *The Apostolic Fathers,* 1:2:301-2 [English], 169 [Greek]); **አግናጢዮስ *ማግኔዢያንስ*** 13:1 (English, 146, and Greek, 115), *Martyrdom of Polycarp,* 14:3 (English, 208, and Greek, 194), Lightfoot, *The Apostolic Fathers,* 2:3:483 [English], and 388 [Greek]). E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches*, 49 **ጠቅሶ እንደ ጻፈው::**

[22] **ይህ የአግናጢዮስ ሙግት በሻርፐስ ሕግ ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 የሚገዛ ስላልሆነ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ማለት ስሕተት ነው::** E. Calvin Beisner *"Jesus Only" Churches*, 49.

ሐዋርያት "ለክርስቶስና ለአብ ታዛዦች ናቸው" (Magnesians, 13:2; Magnesians, inscription; 1:2; 13:1, Ephesians, 21:2; Trallians 1:1; Philadelphians, inscription; 1:1; 3:2; Polycarp, inscription; and Smyrnæans, inscription)[23].

"ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ እንዲሁም በዘመኑ መጨረሻ ላይ የተገለጠ" ያለአባቱ ፈቃድ "አንዳች ነገር ማድረግ የማይችል"። "ከአንዱ ከአብ ዘንድ የመጣ"[24]።

ጶሊቃርጶስ ደግሞ እንዲህ ይላል:—

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት እንዲሁም ዘላለማዊው ሊቀ ካህን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በእምነትና በእውነት ያጽናችሁ" (*Philippians* 12:2).

በርናባስ ደግሞ:—

"ጌታ ለእኛ ነፍስ ሲል ሥቃይን ታገሠ፤ የዓለም ሁሉ ጌታ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር አለ" (*Epistle of Barnabas,* 5:5, 9)[25].

የቤተ ክርስቲያን አበው ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ጽፈዋል።

ቀለሜንጦስ:—

[23] የግሪኩን ቅጅ ከ Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* ላይ ይመለከቷል።
[24] Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* 144-45 (English), 113-14 (Greek)
[25] Lightfoot and Harmer, *The Apostolic Fathers,* 273 (English), 247-48 (Greek)